በፊንፊኔ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በ2012 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የሁለተኛ መንፈቀ ትምህርት ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ትምህርት ሞዴል ፈተና፡፡ለአፋን ኦሮሞ

መመሪያ፡-

- ***መመሪያዎቹን በጥንቃቄ አንብቡ፡፡ ስለ ፈተናው ጥያቄ ካላችሁ ፈተናው ከመጀመሩ በፊት ፈታኙን/ፈታኟን/ መጠየቅ ትችላላችሁ፡፡ ፈተናው ከተጀመረ በኋላ ምንም አይነት ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም፡፡***
- ***ይህ የአማርኛ ትምህርት ፈተና ነው፡፡ የተሰጠው ጊዜ 1 ሰአት ሲሆን ከአንድ ሰአት በላይ መስራት አይፈቀድም፡፡ ከተፈቀደው ጊዜ ቀድማቹሁ ከጨረሳቹሁ የሰራችሁትን ፈተና መከለስ ትችላላችሁ፡፡***
- ***እያንዳንዱ ጥያቄ አራት አማራጮች አሉት፡፡ ጥያቄዎቹንና ምርጫዎቹን በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ መልሳችሁን በሚሰጣችሁ የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ አመልክቱ፡፡ መልሶቻችሁን ለማመልከት ከምርጫዎቹ ስር የሚገኘውን ሳጥን አጥቁሩ/አቅልሙ/፡፡***
  - ***ለምሳሌ፡- መልሳችሁ 2ኛው ምርጫ ከሆነ ከስሩ የሚገኘውን ሳጥን በሚከተለው አኳኋን***
  - ***አጥቁሩ፡፡***

A	B	C	D
☐	■	☐	☐

- ***መልሳችሁን ለመቀየር ከፈለጋችሁ የመጀመሪያውን መልስ በደንብ አጥፉ ከዚያም የተቀየረውን መልሳችሁን አጥቁሩ፡፡***
- ***ፈተናውን ለብቻችሁ መስራት ይኖርባችኋል፡፡ በማንኛውም መንገድ ለማጭበርበር ብትሞክሩ ውጤታችሁ በሙሉ ይሰረዛል፡፡***
- ***ለፈተና የተፈቀደላችሁ ሰዓት ሲያልቅ ፈታኙ/ኟ/ እንድታቆሙ ይነግሯችኋል፤ ወዲያውኑ ማቆም ይኖርባችኋል፡፡***
- ***ፈተናው እንዳለቀ መውጣት አይፈቀድም፡፡ የፈተናው ወረቀቶች እስኪሰበሰቡና ፈታኙ/ኟ/ ፈቃድ እስኪሰጧችሁ መጠበቅ አለባችሁ፡፡***

መመሪያ አንድ

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ከተሰጡት አማራጮች ምረጡ፡፡

1.	እልባት	A.	እልህ	B.	ምክንያት	C.	መፍትሄ	D. ሰበብ
2.	ንትርክ	A.	ንቀት	B.	ጭቅጭቅ	C.	መስማማት	D. ሙግት
3.	ጥንት	A.	ዘንድሮ	B.	አምና	C.	ካቻምና	D. ድሮ
4.	ዘመመ	A.	አጋደለ	B.	ቆመ	C.	ቀጥአለ	D. ጸጥአለ
5.	በኩር	A.	የመጨረሻ	B.	የመጀመሪያ	C.	የመሀል	D. ልጅ

መመሪያ ሁለት

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተቃራኒ ፍቺያቸውን ከተሰጡት አማራጮች ምረጡ፡፡

6.	ምርቃት	A.	ስጦታ	B.	በረከት	C.	እርግማን	D. ተስፋ
7.	የምስራች	A.	መርዶ	B.	ወሬ	C.	መልካም	D. ደስታ
8.	ብልህ	A.	አስተዋይ	B.	አዋቂ	C.	ብልጥ	D. ሞኝ
9.	ግርጌ	A.	ራስጌ	B.	ጎን	C.	ታች	D. አጠገብ
10.	ጠላት	A.	ጓደኛ	B.	ወዳጅ	C.	ባዳ	D. ዘመድ

መመሪያ ሶስት

ከጥያቄ 11-50 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጥ/ጪ/፡፡

11. በቃል እየተነገረ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ .....ይባላል?

A. ልቦለድ B. ተውኔት C. ድራማ D. ስነ-ቃል

12. ተባእት ጸታ አመልካች የሚያመለክተው ተውላጠ ስም የቱ ነው?

A. አንቺ B. እኔ C. አንተ D. እናንተ

13. ፈተና ስላለበት በጠዋት ተነስቷል፡፡ የዚህ አ.ነገር ግስ ገላጭ.....ነው?

A. ስላለበት B. በጠዋት C. ፈተና D. ተነስቷል

14. አጠር ባለ አቀራረብ የሚቀርብና ምርጥ ቃላትን የሚጠቀም.....ነው?

A. ግጥም B. አንቀጽ C. ስንኝ D. ስድ ጽሁፍ

15. አዲሱጤና ጣቢያ በመጪው ዓመት አገልግሎት መስጠት ይጀምራል፡፡ የተሰመረበትቃል...ነው

A. ስም B. ግስ C. የስም ገላጭ D. የግስ ገላጭ

16.“ አል-ም” የሚለውን ቅጥያ በመነሻና በመድረሻ ላይ ሊወስድ የሚችለው ቃል የቱ ነው?

A. ጸሀፊ B. ደራሲ C. ሰአሊ D. ደረሰ

17. ከሚከተሉት ውስጥ ሀረግ የሆነው የቱ ነው?

A. የሚሮጠው ልጅ B. ልጁ ሮጠ C. በሩ ተከፈተ D. ዝናቡ ዘነበ

18. ከስም የቃል ክፍል ሊመደብ የሚችለው የቱ ነው?

A. ሰአሊ B. ስዕል C. ለበሰ D. ሳለ

19.....በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ መነሻ ሀሳብ በመስጠትና የጋራ ሀሳብ ላይ የመድረስ ሂደት ነው

A. ክርክር B. ሙግት C. ውይይት D. ጭውውት

20. ዛሬ በማለዳው ዝናብ **ስላካፋ** ወደ ትምህርት ቤት መሄድ አልቻልኩም፡፡ የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ.....ነው?

A. ስለ ተቆፈረ B. ስለ አባራ C. ስለ ቆመ D. ስለ ዘነበ

21 ከሚከተሉት አንዱ ከስራ ደብዳቤ ስር ሊካተት አይችልም

A. ማመልከቻ B. ማስታወቂያ C. የሰርግ ጥሪ D. ማሳሰቢያ

22. ሲጠብቅና ሲላላ የተለያየ ትርጉም ሊሰጥ የሚችለው ቃል የቱ ነው?

A. ገና B. መላ C. ዘዴ D. በጋ

23. ዘንድሮ የጤፍ ዋጋ **እሳት ሆነ**፡፡የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ.....ነው?

A. ነደደ B. የሚፋጅ ሆነ C. ውድ ሆነ D. ርካሽ ሆነ

24. ሸማግሌዎቹ የሰርጉን ቀን **ቆረጡ**፡፡የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ.....ነው?

A. ተስማሙ B. ወሰኑ C. ተለያዩ D. ቀነጠሱ

25. ዛሬ በጊያሳ ገበያ ሽንኩርት **ጥንቡን ጣለ**፡፡የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ.....ነው?

A. ሸተተ B. ተወደደ C. ከበደ D. ረከሰ

26 .ክርክር በሚደረግበት ጊዜ መደረግ የሌለበት ተግባር የቱ ነው?

A.መረጃዎችንማሰባሰብ B.አለባበስንማስተካከል C. ሀሳብን መደጋገም D.ሰአትን በአግባቡመጠቀም

27. ለአይን ያዘ ሲል .....ማለቱ ነው? A. ማየት አቃተው B. ነጋ C. ታወረ D. ጨለመ

28. ቶሎሳ መጣ ወይ በሚለው ዐ.ነገር መግባት ያለበት ስርአተ ነጥብ የቱ ነው?

A/ :: B/ ? C/ ! D/ ፥

29. ትክክለኛውን የስርአት ነጥብ አገባብ የያዘ ዐ.ነገር የቱ ነው?

A ውይ! ሰአቴን ጣልኩ:: B. ውይ ሰአቴን! ጣልኩ

C. ውይ ጣልኩ ሰአቴን! D .ውይ! ሰአቴን! ጣልኩ

30. ሲጠብቅና ሲላላ የትርጉም ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ቃል የቱ ነው?

A. ጨረሰ B. ቁራሽ C. ቀለለ D. ፍራሽ

31. አንድ ደረሲ ወይም አጥኚ በመረጃ ምንጭነት የሚጠቀምባቸው መጽሃፍት.....ይባላሉ?

A. አባሪ B. ማውጫ C. ዋቢ መጽሃፍት D. ተቀጽላ

32. ድርብ ቃል ወይም ጥምር ቃል የሆነው የቱ ነው?

A. አውሮፓውያን B. አይነ-ደረቅ C. ልጆቻችን D. አካባቢያችን

33 . ከሚከተሉት ውስጥ ዐ.ነገር የሆነው የቱ ነው?

A. ምሳውን በላ B. ስለ መጣ C. እቤት እያለሁ D. ወደ አዳማ

34. እነ ቶሎሳ ከአባታቸው ጋር መጣ፡፡በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ የሚታው ሰዋሰዋዊ ስህተት የ.....ነው?

A, የጾታ B. የቁጥር C. የቅጥያ D. የባለቤት

35. የትላንትናው በአል ጥሩ ነበር ስንበላ፣ ስንጠጣና ስንዝናና ነበር፡፡ በዚህ ዐ.ነገር መግባት ያለበት ስርአተ ነጥብ የቱ ነው?

A. ‹‹ ›› B. .... C. ፤ D. ፣

36. ስለ አንድ ሀሳብ ብቻ የሚናገር ወይም የሚያትት አነስተኛ የጽሁፍ ክፍል.....ይባላል?

A. ሀይለ ቃል B. ግጥም C. ስንኝ D. አንቀጽ

37.ልብሱ ያጠራት.. ...አያስጠላባትም፡፡ በዚህ ዐ.ነገር መግባት ያለበት አያያዥ ቃል የቱ ነው?

A. ስለሆነ B. ቢሆንም C. ከሆነ D. እንደሆነ

38. ግንዛቤን ለማስፋት ረጋ ባለ መንፈስ የምናነበው የንባብ አይነት .....ይባላል?

A .የዝግታ ንባብ B. ሰፊ ንባብ C. የአሰሳ ንባብ D. የፍጥነት ንባብ

39. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ጸጸት ወይም ቁጭት የሚያመለክተው የቱ ነው?

A. ጎሽ! እንኳን መጣህ B. ተው!ብዬሃለሁ C. ባልመጣ ይሻለኝ ነበር! D. እንዴት ያምራል!

40. ለባቄላ ሰበረ ካለ ለማር..... ይላል

A. አጠነ B. ቀጠፈ C. ሸመጠጠ D. ቆረጠ

41. ለበሬ በረት ካለ ለፍየል.....ይላል

A. ቆጥ B. ቤት C. ግርግም D.ጉሮኖ

42. ደራርቱ ጥቁር አልማዝ ናት፡፡ የዚህ ዐ.ነገር የስም ገላጭ.....ነው?

A. አልማዝ B. ጥቁር C. ደራርቱ D. ናት

43. ከሚከተሉት ውስጥ የተዋጠ ድምጽ ያለው የቱ ነው

A. በአሜሪካ B. በአለም C. በአገሩ D. ያባቴ

44. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ ትክክለኛውን የስርአተ ነጥብ አገባብ የተከተለ የቱ ነው?

A. “ለሰው ሞት አነሰው” አለች ቀበሮ፡፡ B. “ ለሰው ሞት አነሰው አለች ቀበሮ”፡፡

C. ለሰው “ሞት” አነሰው አለች ቀበሮ፡፡ D. “ለሰው ሞት” አነሰው አለች ቀበሮ፡፡

45. የምክንያትና የውጤት ትስስርን የሚያመለክተው ዐ.ነገር የቱ ነው?

A. ኮሮና የአለማችን ወረርሽኝ በሽታ ነው፡፡ B. ራሳችንን ከኮሮና እንጠብቅ

C. ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ በርካታ ሰዎች በቫይረሱ ተያዙ፡፡ D. ርቀታችንን እንጠብቅ

46. እኔና እሱ ወንድማማች..... A. ናቸው B. ነው C. ነን D. ነኝ

47 ቤቶች በሚለው ቃል ያለው ቅጥያ.....ነው?

A. -ኦች B. -ች C. -ኡ D. ቤት

48. ከግስ የቃል ክፍል ሊመደብ የሚችለው የቱ ነው?. A. ሰው B. ብርቱ C. ነው D. ወደ

49. ገጠመ ብሎ ገጣሚ ካለ ዘመረ ብሎ.....ይላል

A. መዝሙር B. ዘማሪ C. መዘመር D. ዘመረ

50. አቀበቱን.....ቁልቁለቱን.....ውሎ መጣ

A. ሲሄድ፡ሲመጣ B. ሲመጣ ሲወርድ C. ሲወጣ ሲወርድ D. ሲወርድ ሲወጣ

መመሪያ አራት

ከጥያቄ 51-53 በጅምር የቀረቡትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚያሚሉትን አባባሎች ከተሰጡት አማራጮች ምረጡ

51. ደፋርና ፄስ.....

A.መውጫ አለው B. መውጫ የለውም C. ብልሃት አለው D. መውጫ አያጣም

52. ሌባ ላመሉ..... A.ዳቦ ይልሳል B. ዳቦ ይለምናል C. ዳቦ ይወዳል D. ዳቦ ይሰርቃል

53. ድር ቢያብር..... A. ነብር ያስር B. ዝሆን ያስር C. አንበሳ ያስር D. ሰው ያስር

መመሪያ አራት

ከጥያቄ 54-57 ድረስ ያሉትን በግጥሙ መሰረት መልሱ

ተባበር ተባበር፣ ተው አትለያይ፣

ድር አንበሳ ያስራል፣ ሲሆን አንድ ላይ፡፡

ካይምሮህ ውስጥ ይውጣ፣ ይሰረዝ ቅናት፣

እሱ ያለ እንደሆን ፣አይሰራም ቤት፡፡

ትልቁ ትንሹ፣ ሲሆን አንድ ላይ፣

ሁሉ እኩል ይሰራል፣ ሳይኖር የሚለይ፡፡

ድር ሲያስር ፣አንበሳን በመተባበር፣

የሰው ልጅ አንድነት፣ ይጠቅማል ላገር፡፡

ምሳሌው ልክ ነው፣ ለሰው ልጅ ተስማሚ

በህሊናህ ጻፈው፣ አድርገው ቀዋሚ፡፡

ባንድነት ተማክሮ፣ ተባብረው ቢሰሩ፣

ክፉ ደግ ይሆናል፣ ጠፍቶ መቃቃሩ፡፡

54. ግጥሙ.....ስንኞችና.....ሀረጎች አሉት?

A. 12፣24 B. 12፣10 C. 12፣12 D. 13፣14

55. በአራተኛው ስንኝ እሱ ያለ እንደሆን የተባለው ምንድነው?

A. ትዕቢት B. ቅናት C. ተንኮል D. ውሸት

56. በህሊናህ ጻፈው አድርገው ቀዋሚ የሚለው ስንተኛ ስንኝ ነው?

A. 10 B. 12 C. 16 D. 5

57. የግጥሙ የመጨረሻ ቤት መድፍያ ቃል .....ነው?

A. ተስማሚ B. መተባበር C. ቢሰሩ D. መቃቃሩ

መመሪያ አምስት

ከጥያቄ 58-60 ድረስ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

ቀናትና ሳምንታት ተደምረው ወራቶች ሲመጡ፣ወራቶች ተያይዘው አመታት ሲሆኑ፣አመታት ተደምረው ዘመን ሲከሰት ያልለመድናቸውና የማናውቃቸው ክስተቶች አብረው ብቅ ይላሉ።እስከ ዛሬ ድረስ እንደ ምናውቀው በመተቃቀፍ፣ በመጨባበጥ፣ በመሳሳም ሰላምታ መለዋወጥ እንዲሁም አበሮ መስራት፣ አብሮመብለት፣ ሀዘንና ደስታን አብሮ መካፈል የመሳሰሉት ይዘን የቆየነው የባህላችን መልካም ገጽታዎች ናቸው።ይሁንና ይህ የዕለት ተዕለት ክንውናችን አሁን በአለምና በሀገራችን በተከሰተው ኮቪድ19 /ኮሮና ቫይረስ/ወረርሽኝ ዋና መተላለፊያ መንገድ ስለሆነ ስንተገብረው የቆየውን እንቅስቃሴያችንን ለጊዜው በመተው ጊዜው የሚጠይቀውን የጤና ባለሙያዎችን ምክርና መንግስት የሚሰጠንን መመሪያ ማለትም እጅን በሳሙናና በውሃ መታጠብን፣ አለመጨባበጥን፣ አለመተቃቀፍን፣ ርቀት መጠበቅን የመሳሰሉትን በመተግበር በፊታችን ያለውን የብልጽግና ጊዜ እያየን ወደ ፊት መጓዝ አለብን።

58. በምንባቡ መሰረት ጊዜና ዘመን.....ይሆናሉ?

A. አንድ ቦታ ይቆማሉ B. ይለዋወጣሉ C. ይመሳሰላሉ D. ሁሌም አንድ ናቸው

59 ጊዜው የሚጠይቀውን መተግበር አለብን ሲል.....ማለቱ ነው?

A. መተቃቀፍ B. መጨባበጥ C. መሳሳም D. አለመጨባበጥ

60. የምንባቡ ርዕስ ምን ሊሆን ይችላል?

A. መልካም ስራ B. ጊዜና ዘመን C.ባህል D. መተባበር

አዘጋጅ፡- መ/ርት ወላንሳ ተካበ

የጥያቄዎች መልስ

1. C
2 .B
3. D
4. A
5. B
6 .C
7 .A
8. D
9. A
10. B
11. D
12. A.
13. B
14. A
15. C
16. D
17. A
18. B
19. C
20. D
21. C
22. A
24. B
25. D
26. C
27. D
28. B
29. A
30. D
31. C
32. B
33. A
34. B
35. C
36. D
37. B
38. A
39. C
40. D
41. D
42. B
43. C
44. A
45. C
47. A
48. C
49. B
50. C
51. D
52. A
53. C
54. A
55. B
56. A
57. D
58. B
59. D
60. B

23. C

46. C